ማርች 26ቀን 2020ዓ.ም.

ውድ ቤተሰቦች፡-

የIndividualized Education Programs (IEP) እና 504 እቅዶች ተማሪዎችን ጨምሮ ሁሉም ተማሪዎች የትምህርት ቁሳቁሶች እና እንቅስቃሴዎች ማድረጊያ ማግኘት እንዲችሉ ለማድረግ የFCPS ሰራተኞች የርቀት ትምህርት ቁሳቁሶችን ለማዘጋጀት ጠንክረው እየሠሩ ናቸው ፡፡ ትምህርት ቤቶች ከፌደራል ሕግ ጋር በሚጣጣም መልኩ የርቀት ትምህርትን እንዲያቀርቡ ለመርዳት የዩናይትድ ስቴትስ የትምህርት ክፍል (USDOE) የአካል ጉዳት ያላቸውን ተማሪዎች ለመርዳት የተለየ የትምህርት ነባራዊ ሁኔታዎችን ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት የትምህርት አገልግሎቶች እና ድጋፎች ሁኔታዎች ላይ ተጽዕኖ ሊያሳድር እንደሚችል ተገንዝቧል ፡፡ ልዩ ትምህርት እና ተዛማጅ አገልግሎቶች ለእያንዳንዱ ተማሪ አግባብነት ባለው መንገድ  በርቀት ትምህርት ሆኖ በድህረ ገጽ እና/ወይም በስልክ ሆኖ በርቀት ሞዴሎች አማካይነት ሊደረሱ ለሚችሉ ተማሪዎች ተገቢ ትምህርት እና ተዛማጅ አገልግሎቶች ይሰጣሉ ፡፡

ከ 30 ማርች 30ቀን ጀምሮ FCPS ለለአስተማሪዎች የልዩ ትምህርት መምህራን እና ተዛማጅ አገልግሎት ሰጭዎችን ጨምሮ ለሁሉም የርቀት ትምህርትን ለመዘጋጀት እንዲችሉ እና ከተማሪዎቻቸው ጋር እንደገና እንዲገናኙ የርቀት ትምህርት ስልጠና ይጀምራል፡፡ ከመዋእለ-ህጻናት ትምህርት በፊት ጀምሮ እስከ አስራ ሁለተኛ ክፍል ላሉ ተማሪዎች ቀጣይነት ያለው የትምህርት መርጃዎች እና መጠቀሚያዎች የተዘጋጀ ሲሆን በጥቁር ሰሌዳ እና በFCPS የህዝብ ድህረ ገጽ ላይ ተለጥፏል።

Https://www.fcps.edu/news/coronavirus-update-academics-distance

በተጨማሪም ተማሪዎች በቤታቸው ሆነው እንዴት ድጋፍ ማግኘት እንደሚችሉ የሚያሳይ የድጋፍ መስጫ ሳጥኖች ተዘጋጅተዋል። ብዙ ከአካለ ጉዳት ጋር የተዛመዱ ማስተካከያዎች እና አገልግሎቶች ውጤታማ በሆነ መንገድ በድህረ ገጽ አማካኝነት ሊሰጡ ይችላሉ። ይህ ለምሳሌ ለቤት ስራዎች የሚሰጠውን የጊዜ ማራዘሚያ ፣ የቤት ስራዎች ማስተካከያ፣ ትክክለኛውን ምስል የሚያሳይ ተንቀሳቃሽ ምስል ወይም ተተኪ የምልክት ቋንቋ አስተርጓሚ ፣ ተደራሽ የንባብ ቁሳቁሶች እና በተንቀሳቃሽ ምስል ስብሰባ አማካኝነት የሚሰጡ የንግግር ወይም የቋንቋ አገልግሎቶችን  ሊያካትቱ ይችላሉ፡፡ ይህንን በዚህ ድህረ ገጽ ላይ የሚገኘውን የመጠቀሚያ መሳሪአዎች ሳጥን እንዴት ልንጠቀምበት እንደምንችል የሚያሳይ ተንቀሳቃሽ ምስል ስላዘጋጁልን ለFairfax County የወላጆች እና አስተማሪዎች ማህበር የተለየ ምስጋና እናቀባለን ። https://youtu.be/RlHKjSWIgr8

አስተማሪዎች በርቀት ሆነው ወደ መሥራት ሲመለሱ ት/ቤቶች ልዩ ትምህርትን በሚመለከት የርቀት ስብሰባዎችን/ቴሌኮንፈረንስ እና ጥቁር ሰሌዳ/Blackboard Collaborate Ultra/ በመጠቀም ከወላጆች ጋር ውይይት ያካሄዳሉ። ይህ መደበኛ ለልዩ ትምህርት መመልመልን ፣ የብቁነት እና እንደየአስፈላጊነቱ የIEP ስብሰባዎች ማካሄድን ያጠቃልላል። የልዩ ትምህርት ጉዳይ ሥራ አስኪያጆች ግለሰባዊ አገልግሎቶችን ለተማሪዎች ለማቅረብ የሚረዱ ዘዴዎችን ያዘጋጃሉ፡፡

የፌዴራል ፣ የክልል እና የFCPS አመራሮች በዚህ ብሔራዊ የአደጋ ጊዜ ወቅት ትምህርት ቤቶች በተለምዶ በጤና እና ደህንነት ስጋቶች ምክንያት የሚሰጡትን ሁሉንም አገልግሎቶች መስጠት እንደማይችሉ ይገነዘባሉ፡፡ አስተማሪዎቻችን አስፈላጊ የሆኑትን ነገሮች በማስተካከል ፣ በማሻሻል እና በመማር ለተማሪዎችዎ ትርጉም ያለው የትምህርት ተሞክሮዎችን/ሂደቶችን ለመፍጠር የሚሰሩ ባለሞያ አስተማሪዎች ናቸው፡፡ እኛ ከእርስዎ እና ከልዩ ትምህርት አጋሮቻችንም ጥያቄዎችን ሰምተናል ፡፡ በአሁኑ ጊዜ ሁሉም መልሶች ባይኖረንም በሚቀጥሉት ሳምንቶች በተደጋጋሚ ለሚጠየቁ ጥያቄዎች መልስ መስጠት (መለጠፍ) ላይ እንሰራለን ፡፡ በወረዳችን እና በማህበረሰባችን ሁሉ ከጥቂት ሳምንቶች በፊት ባላሰብንበት መንገድ ተፈታታኝ ሁኔታ ገጥሞናል።

ይህንን የርቀት ትምህርት ተልእኮ ስንጀምር ትምህርት ቤታችን እና አስተማሪዎቻችን ከእርስዎ ጋር ይገናኛሉ። ስለ እገዛዎ እና ግንዛቤዎ አመሰኛለሁ።

ከልብ:-

Teresa Johnson
ረዳት ዋና ሃላፊ
ልዩ አገልግሎት Fairfax County የህዝብ ትምህርት ቤት